# ብራዚል በኢትዮጵያ የምግብ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸዉ ስደተኞች 18 ቶን የምግብ ልገሳና 65 የውሃ ማጣሪያዎችን ሰጥታለች።

አዲስ አበባ፣ የካቲት 17፣ 2024

የብራዚል መንግስት የምግብ እርዳታና የውሃ ማጣሪያዎችን በኢትዮጵያ በጋምቤላ ክልል ለሚኖሩ ስደተኞችንና የአካባቢ ማህበረሰቦችን ለመደገፍ መለገሱን አስታወቀ። ጋምቤላ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ የስደተኞች ማስተናገጃ ክልል ሲሆን በዋናነት ከደቡብ ሱዳን የመጡ 385,000 ስደተኞች ይኖሩበታል።

የተከበሩት የብራዚል ቀዳማዊት እመቤት ጃንጃ ሉላ ዳ ሲልቫ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት፣ በቀን 5,600 ሊትር ዉሃ የማጣራት አቅም ያላቸው 65 የውሃ ማጣሪያዎችንና፣ 18 ቶን የምግብ አቅርቦቶች ለግሰዋል።

የብራዚል መንግስት ረሃብና ድህነትን ለመቀነስ አለም አቀፋዊ ትብብርን እየመራች ስትሆን፣ ለስደተኞችና በአፍሪካና በአለም ላሉት አካባቢ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር ለመፍታት ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማግኘት ጥረት እያደረገች ነዉ።

በስጦታ ስነ-ስርዓቱ ላይ የብራዚል ቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ጃንጃ ሉላ ዳ ሲልቫ “ለብራዚል በአፍሪካ ውስጥ ረሃብንና ድህነትን መዋጋት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በብራዚል እና በኢትዮጵያ ውስጥ ጨምሮ በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ የረሃብ ሁኔታ ዉስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች መጠለያዎች ውስጥ አሉ። እነዚህን ተግዳሮቶች መፍታት የምንችለው በትብብር እና በመተሳሰብ ሲሆን የመፍትሄ ሃሳቦችን በጋራ በመስራት ረሃብንና ድህነትን ከአለም ላይ ለማጥፋት ስንሞክር ብቻ ነው” ብለዋል።

በብራዚል የትብብር ኤጀንሲ (ኤቢሲ) የሰብአዊ ትብብር አጠቃላይ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ጆሴ ሶላ " እነዚህ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ወደፊት የሚደረጉ ተግባራት፣ ከብዙዎቹ የመጀመሪያ ሲሆኑ፣ ስደተኞች ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉበት ጊዜ እና እነሱን በሚቀበሏቸው የአካባቢ ማህበረሰቦች ደህንነት ላይ የበኩላቸውን መልካም አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ተስፋ እናደርጋለን" ብሎ ተናግረዋል።

ይህ የምግብ ድጋፍ እንዲሁም ማጣሪያዎቹ፣ ለጋምቤላ በሚገኙት በፒንዩዶ፣ ጁዊ፣ ንጉዌኒኤል፣ ቲየርኪዲ እና ኩሌ የስደተኞች መጠለያ ካምፖች ውስጥ ሕሙማንን ጨምሮ ነፍሰ ጡር እና የሚያጠቡ እናቶችን፣ ለአደጋ የተጋለጡ ሕፃናትና ስደተኞችን ጨምሮ ለሴቶችና ልጃገረዶች እጅግ አስፈላጊ ድጋፍ ይሆናቸዋል። ዕርዳታው በቅርቡ ከሱዳንና ከደቡብ ሱዳን በተነሱት ግጭቶች እና ማኅበረሰቦዊ ቀዉሶች ምክንያት ለመጡትም ያካትታል።

የኢፌዲሪ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጠይባ ሀሰን በተደረገዉ ልገሳ ምስጋና አቅርበዋል። ወይዘሮ ጠይባ “አሁን እየተደረገ ያለው ድጋፍ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸዉ ሰዎች ትልቅ ትርጉም አለው ። በዚህ ረገድ እንግዳችንን - ቀዳማዊት እመቤትን በማመስገን ትልቅ ክብር ይሰማኛል”።

ክብርት ወይዘሮ ጠይባ ሲናገሩ “በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክያት የሚፈናቀሉ ሰዎች በምድር ላይ እንደሚኖር ማንኛውም ሰው የተሻለ የዕለት ተዕለት ኑሮ የመኖር መብት ስላላቸው፣ ለሚመለከቷቸው ሰዎች ፍላጎቶች የተሻለ ምላሽ እንዲሰጡን እንደዚህ አይነት ድጋፍ ሰጪ እጆችን በደስታ እንቀበላለን። ስለዚህ እንደዚህ ያሉ ውጥኖች በሚቀጥሉት ዓመታት ሰፋ ባለ መልኩ ሊደገሙ እንደሚችሉ ጽኑ እምነት አለን።

“ቀዳማዊት እመቤት ሉላ ዳ ሲልቫ እና የብራዚል መንግስት በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች ላደረጉት ልግስናና ደግነት እናመሰግናለን። ይህ በተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና በምግብ እጦት ለተቸገሩ በሺዎች ለሚቆጠሩ ስደተኞች የህይወት አድን ድጋፍ ያደርጋል” ሲሉ በኢትዮጵያ የዩኤንኤችሲአር ተወካይ አቶ አንድሪው ምቦጎሪ ተናግረዋል። "ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ለስደተኞች እና በግዳጅ ለተፈናቀሉ ወገኖች መፍትሄ ለመስጠት ከብራዚል ጋር ፍሬያማ ትብብር እንደሚያጠናክር ተስፋ እናደርጋለን" ብለዋል ።

ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ከሚባሉት ስደተኞችና ተፈናቃዮች ከሚቀበሉ ሃገራት መካከል አንዷ ነች። በአፍሪካ ሶስተኛዋ ትልቁ የስደተኞች አስተናጋጅ ሀገር እንደመሆኗ በአሁኑ ወቅት ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች በብዛት የሚገኙባት ሲሆን በተለይም ከደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ኤርትራና ሱዳን የተውጣጡ እንዲሁም ወደ 3.5 ሚሊዮን የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ ተፈናቅለዋል።

የብራዚል መንግስት ለUNHCRና አጋሮቹ ያደረገዉ ልገሳ ወሳኝ ጊዜ ላይ ነዉ የመጣዉ።

የአየር ንብረት ቀውሱ በአለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ምርትን እና ስርጭትን እየተፈታተነ ባለበት ወቅት ፣ ይህ ልገሳ የስደተኞችን እና አካባቢ ማህበረሰቦችን አስቸኳይ ፍላጎቶችን ለማሟላት አስተዋጽኦ። እነዚህ የዉሃ ማጣሪያዎች በዉሃ ወለድና ንጽህና ጉድለት ምክኛት የሚከሰቱ በሽታዎችን በማስወገድ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጾ ዬኖራቸዋል።

**ለበለጠ መረጃ፡-**

በአዲስ አበባ፣ ሉክሪዚያ ቪቶሪ፣ vittori@unhcr.org፣ +251 97 810 4031 / አቶ ስለሺ ደሚሴ ፡ sileshiD@rrs.gov.et፣ +251 912 023 969

በናይሮቢ (ክልላዊ መስሪያ ቤት)፣ እምነት ካሲና፣ kasina@unhcr.org፣ +254 113 427 094

በብራዚሊያ፣ ሚጌል ፓቺዮኒ፣ pachioni@unhcr.org፣ +55 11 98875 3256